810 መ250/38
29/02/2011

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Urban Development & Construction

755/2013

ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ
ከ/ል/ኮ/ሚ/ር

ጉዳዩ፡-**የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ**

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የፓናል ውይይት ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 67/2011 ሆኖ ከጥቅምት 29 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል የጸደቀ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም የጸደቀው 1 (አንድ) ጥራዝ ሰነድ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ የተላከ ስለሆነ በመመሪያው መሠረት እንዲፈጸም አስታውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ጃንጥራር አባይ ይግዛው
ሚኒስትር

ግልባጭ፡

- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ( የቤቶችና መሠረተ ልማት ዘርፍ)
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ (የከተማ ልማት ዘርፍ)
- ለሚኒስትር ጽ/ቤትና ሚኒ-ካቢኔ ጉዳዮች ቢሮ
- ለሕግ  አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

ከ/ል/ኮ/ሚ/ር

# የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም
ETHIOPIAN URBAN FORUM

## የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም
## የፓናል ውይይት ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 755/2013

ጥቅምት/2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ፣

በኢትዮጵያ ፈጣን የከተሞች ዕድገትን ተከትሎ የከተማ ነዋሪዎችንና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ እና ትብብር በማጠናከር፣ መልካም ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በማስፋፋት፣ እንዲሁም የከተሞችን እሴቶች በማስተዋወቅና በማጎልበት ጠንካራ መሰረት ያለዉ የከተማ ህዝብ ንቅናቄና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ በየዓመቱ የከተሞች ሣምንት በሚል ሲከበር የቆየ ሲሆን ከ2007ዓ.ም. ጀምሮ የኢትዮጵያ የከተሞች ፎረም በሚል መከበር የጀመረ ሲሆን ይህ የከተሞች ፎረም በየዓመቱ ሳይሆን በየሁለት ዓመት እንዲከበር በመወሰኑ በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም እንደወቅታዊ ሁኔታው የሚለዋወጡ መሪ ቃሎችን በመጠቀም ይከበራል፡፡

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ዓላማን ለማሳካት ከሚከናወኑት ዋና ዋና ተግባራት መካከል የሴሚናርና የፓናል ውይይት ዝግጅት አንዱ ነው፡፡ በዚህ ዝግጅት በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የተቀረጹ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች አፈጻጸምና ተግዳሮቶች ላይ እና ከዘርፉ ስራዎች ጋር ተዛማጅ የሆኑ የጥናት ጽሁፎች የሚቀርቡ ሲሆን በዘርፈ ብዙ ጉዳዮችና በተመረጡ የዘርፉ ዋና ዋና አጀንዳዎች ላይ የፓናል ውይይት ይካሄዳል፡፡

እነዚህ የፓናል ውይይቶች የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን የትኩረት መስክ በሆኑት የከተማ ልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ዙሪያ በከተማ ልማት ባለድርሻ አካላት ዘንድ የጋራ መግባባትን እና ትክክለኛ ግንዛቤን ለመፍጠር ከሚኖራቸው ከፍተኛ ፋይዳ አንጻርም በርካታ አካላት ተሳታፊ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ በዚሁ መሠረት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ከፍተኛ አመራሮች፣ የቢሮ ኃላፊዎች፣ዳይሬክተሮች፣ የክልል እና የሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ቢሮ ኃላፊዎችና ምክትል ኃላፊዎች፣ የሥራ ሂደት ባለቤቶች፣ የከተማ ከንቲባዎችና ስራ አስኪያጆች፣ተጋባዥ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተወካዮች፣የክልል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ኃላፊዎች፣የክልል የሙያብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ኃላፊዎችና በማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ሙያዎች የባለሙያዎች ምዘና ወቅት ከፍተኛ ተሳትፎ ያደረጉ የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ

የተለያዩ ሃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ ፎረሙ ከሚካሄድበት ከተማ አስተዳደር ልዩ ልዩ ክፍሎች የተመረጡ ነዋሪዎች፣ በከተማው አቅራቢያ ከሚገኘው ዩኒቨርሲቲ የተመረጡ ተማሪዎች፣ በከተማ ልማትና ቤቶች ጉዳዮች ዙሪያ የሚሰሩ የሲቪል ማህበራት፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና የተለያዩ እህት ከተሞች ጥሪ የተደረገላቸው ተጋባዥ እንግዶች በዚህ ውይይት ላይ የሚገኙ ይሆናል፡፡

በመሆኑም ይህንኑ የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ላይ የሚካሄደውን የፓናል ውይይት ግልጸኝነትና አሳታፊነት ባለው መልኩ ለማስፈጸም እና ከፓናል ውይይቱ የሚጠበቀውን ውጤት ለማግኘት እንዲረዳ ይህ የማስፈፀሚያ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር2

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ፣

ይህ መመሪያ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የፓናል ውይይት ዝግጅት መመሪያ ቁጥር 755/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. የተፈፃሚነት ወሰን፣

ይህ መመሪያ በየሁለት ዓመቱ በሚካሄደው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

### 3. የመመሪያው አስፈላጊነት፣

ይህ መመሪያ በየሁለት ዓመቱ በሚካሄደው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ላይ የሚከናወነውና አንዱ ክፍል የሆነው የፓናል ውይይት አፈጻጸም ግልጽና ሁሉን አካላት አሳታፊ በሆነ መልኩ የተመረጡናመድረኩን የሚመጥኑ ጥራት ያላቸው ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበው ውይይት እንዲደረግባቸውና ከውይይቱም ጠቃሚ ግብዓቶችን ለማግኘት አስፈላጊነቱ የጎላ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪ የፓናል ውይይት መድረኩን ለማዘጋጀት የሚፈጸሙ ልዩ ልዩ ክፍያዎችም ተጠያቂነት ባለው መልኩ እንዲፈፀሙ ለማስቻል ነው።

### 4. ከፓናልውይይቱየሚጠበቁውጤቶች፣

1) በሚቀርቡት የጥናት ጽሁፎች የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ አጀንዳዎች ተግዳሮቶች ዙሪያ በቂ ውይይት በማድረግ በቀረቡት መፍትሄዎች ላይ ተግባብቶ ወደ ስራ በመለወጥ የተሻለ የከተማ አገልግሎት ለመስጠት የሚቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል፣
2) በሴክተሩ የተመዘገቡ ውጤቶች ላይ የጋራ መግባበባት ላይ ለመድረስና የተሻሉ ተሞክሮዎችን ለማስፋት
3) በከተሞች፣ በከተማ ልማት ባለድርሻ አካላትናበከተማ ነዋሪው መካከል የመረጃ፣ የእውቀትእና የልምድ ልውውጥ ይካሄዳል።

4) በተመረጡት የፓናል ውይይት ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ መግባባትና ግንዛቤ ይፈጠራል፡፡

5) በሴክተሩ የተቀረጹና ወደ ተግባር የተሸጋገሩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ለማዳበር ጠቃሚ የሆኑ ግብዓቶች እንደሚገኙበት ይጠበቃል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የፓናል ውይይቱ ርዕሰ ጉደዮች

## 5. በፓናል ውይይቱ የሚቀርቡ ርዕሰ ጉዳዮች፣

በፓናል ውይይቱ የሚቀርቡት ርዕሰ ጉዳዮች በሚከተሉት ሦስት ክፍሎች የሚካተቱ ይሆናሉ፡-

1) በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሴክተር ዋና ዋና ምሰሶዎች/Pillars/ መሰረት በማድረግ የተቀረጹ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ይዘትና የትግበራ ሂደት ላይ ያጠነጠኑ ጥናታዊ ጽሁፎች ሲሆኑ፣ እነዚህም፡-

ሀ/ የከተማ የሥራ እድል ፈጠራና የምግብ ዋስትናን በተመለከተ (በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማትስትራቴጂ እና በስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ይዘትና አተገባበር) ዙሪያ የተዘጋጁ ጥናታዊ ጽሁፎች፣

ለ/ በከተሞች ልማታዊ መልካም አስተዳደር እና የከተሞች ፋይናንስ በከተሞች ጽዳትና ዉበት ዙሪያ (የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም የአረንጓዴነት ልማትና ውበት ስትራቴጂ ይዘትና አተገባበር ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች፣

ሐ/ የከተማ እና የገጠር መኖሪያ ቤቶችና የተቀናጀ መሰረተ-ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ይዘት እና አተገባበር ዙሪያ የተዘጋጁ ጽሁፎች፣

መ/ በመሬት ልማት እና ማኔጅመንት ፖሊሲና ስትራቴጂ ይዘትና አፈጻጸም ዙሪያ እና በከተማ ፕላን/መሬት አጠቃቀም ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶችና የተዘጋጁ ጽሁፎች፣ የተዘጋጁ ጽሁፎች፣

2) ከሀገር ውስጥ እና ከውጪ ሀገራት የተገኙ ተሞክሮዎች ላይ ተመስርተው የተዘጋጁ ጥናታዊ ጽሁፎች፣

3) በባለብዘርፍ ጉዳይ ላይ ተመርኩዞ በፓናሊስቶች የሚቀርብ ፓናል ውይይት እንዲሁም

4) በሣምንቱ ውስጥ በአንዱ ቀን ከሰዓት በኋላ በከተማው ሴክተር የሴቶች ተሳትፎን የሚያጠናክር ልዩ የፓናል ውይይት መድረክ ይዘጋጃል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1-4 የተዘረዘሩት እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ርዕሰ ጉዳዮች ሊተኩ ይችላሉ፡፡

## 6. ለፓናል ውይይት የሚቀርቡ ጽሁፎች አመራረጥ፣

1) ለፓናል ውይይቱ የሚቀርቡ ጽሁፎች በዘርፉ የተቀረጹ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ላይ እና አተገባበሩ ላይ የተለያዩ ጽሁፎችንና አስተያየቶችን በማቅረብ  የሚታወቁና በዓለም አቀፍ ደረጃም የተለያዩ ጽሁፎችን በኢትዮጵያ ከተሞችና የሌሎች ሀገሮች ከተሞች ተሞክሮ ማቅረብ ላይ ልምድ ያላቸውን ግለሰቦችና ድርጅቶች በቀጥታ በመጋበዝ የሚመረጥ ይሆናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ለፓናል ውይይቱ የተመደበው ጊዜ ተጨማሪ ጽሁፎችን ለማቅረብ የሚፈቅድ ሆኖ ሲገኝ በውድድር የሚጋበዙ ጽሁፍ አቅራቢዎች ጥናታዊ ጽሁፋቸውን እንዲያቀርቡ ዕድል ይሰጣል፡፡

3) ጥናታዊ ጽሁፍ እንዲያቀርቡ የሚጋበዙ ተመራማሪዎች ወይም ምሁራን ሲኖሩ ራሱን የቻለ የማወዳደሪያ መስፈርት ተዘጋጅቶና በመስፈርቱ መሰረት ተወዳድረው ይመረጣሉ፡፡

## 7. የፓናል ውይይት መድረክ አወያዮች (Moderators) በተመለከተ፣

1) የፓናል ውይይቱ ለሚካሄድባቸው ስድስት ቀናት በሁሉም የመወያያ አዳራሾች ከሚቀርቡት ጥናታዊ ጽሁፎች ጋር ተዛማጅ ዕውቀት ያላቸው አወያዮች ይመደባሉ፣

2) ለፓናል ውይይት መድረክ የሚመደቡ አወያዮች በፓናል ውይይት አስተባባሪ ንዑስ ኮሚቴ አቅራቢነት በኢትዮጵያ የከተሞች ፎረም ዝግጅት አብይ ኮሚቴ እየፀደቁ እንዲመደቡ ይደረጋል፣

3) ከፕሌኔሪ የውይይት መድረኮች ውጪ ባሉት ቀናት ጥናታዊ ጽሁፍ በሚቀርብባቸው አዳራሾች አንድ ለፓናል ውይይት መድረክ የሚመደብ አወያይ አንድ ጥናታዊ ጽሁፍ ያወያያል፣

## 8. በከተሞች ፎረም የቀረቡ ጥናታዊ ጽሁፎች ፕሮሲዲንግ ስለማዘጋጀት

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎም ፕሮሲዲንግ ዝግጅት ደረጃውን በጠበቀና በሀገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በዘርፉ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሁፎችን ይዞ የሚቀርብ ሰነድ መሆኑን በሚገልጽ ደረጃ ለማዘጋጀት እንዲቻል የሚከተሉት ሁኔታዎች እንዲከናወኑ ይደረጋል።

1) የፕሮሲዲንግ አዘጋጅ በግገር እንዲቀርብ ይደረጋል፣

2) የፕሮሲዲንግ ህትመቱን እና የዝግጅቱን ጥራትና ተገቢነት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ ስር የሚገኘው የጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ኃላፊነቱን ተረክቦ ፎረሙ ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ የሚከታተለው ይሆናል፣

3) ለፕሮሲዲንግ ህትመት በጀቱ ከከተሞች ፎረም የሚያዝ ሆኖ የህትመትና ፕሮሲዲንግ አዘጋጅ ወጪ ግምት በፓናል ውይይት ንኡስ ኮሚቴ ዕቅድ ሰነድ ላይ አብሮ የሚቀርብ ይሆናል፣

## 9. በፎረሙ ላይ ጥናታዊ ጽሁፍ ስለሚያቀርቡ ምሁራን ዕውቅና አሰጣጥ

1) በየሁለት ዓመቱ በሚካሄደው የከተሞች ፎረም ላይ በተደረገው ጥሪ /ግብዣ/ መሰረት ጥናታዊ ጽሁፍ ለሚያቀርቡ ምሁራን ከሚከፈላቸው ገንዘብ በላይ ጠቃሚና ሳቢ በመሆኑ ዕውቅና መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ ልዩ ሰርተፊኬት በማዘጋጀት ዕውቅና ይሰጣቸዋል።

ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር6

# ክፍል ሦስት
# ክፍያዎችን በተመለከተ

## 10. ልዩ ልዩ ክፍያዎችን በተመለከተ፣

1) ለፓናል ውይይት ጽሁፋቸውን እንዲያቀርቡ የተመረጡ አቅራቢዎች የመጓጓዣ ወጪ የደርሶ መልስ የአይሮፕላን ትኬት ወጪን እና ከፓናል ውይይቱ ጋር ተያይዞ ፎረሙ በሚካሄድበት ከተማ በሚቆዩበት ጊዜ የመኝታና የምግብ ወጪያቸው በሙሉ መስተንግዶ (Full Accommodation) ይሸፈንላቸዋል፡፡

2) የአይሮፕላን አገልግሎት ከሌለባቸው ቦታዎች የሚመጡ ወይም የተወሰኑ ጉዞዎችን በየብስ ትራንስፖርት ለሚያደርጉ ጽሁፍ አቅራቢዎች በሚያቀርቡት ህጋዊ የትራንስፖርት ደረሰኝ መሠረት ይወራረድላቸዋል፣ የመንገድ ላይ ቆይታ የውሎ አበል የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ዝግጅት በሚወሰነው የቀን ውሎ አበል መጠን መሰረት የሚሸፈን ይሆናል፡፡

3) የፓናል ውይይት መድረክ አወያዮች እና የፓናል ተጋባዥ ፓናሊስቶች የደርሶ መልስ የአይሮፕላን ትኬት ወጪያቸው እንዲሁም ከውይይቱ ጋር በተያያዘ ፎረሙ በሚካሄድበት ከተማ ለሚቆዩበት ጊዜ የምግብና የመኝታ ወጪያቸው በሙሉ መስተንግዶ (Full Accommodation) ይሸፈንላቸዋል፡፡

4) ፎረሙ ከሚካሄድበት ከተማ ተጋባዥ ለሆኑ 200 ተሳታፊዎች የምሣና የትራንስፖርት አበል ይከፈላቸዋል፡፡ የክፍያው መጠን የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የፋይናንስ አፈጻጸም መመሪያ ላይ በተገለፀው መሠረት ይሆናል፡፡ የተሳታፊዎችን ዝርዝር ፎረሙ የሚካሄድበት ከተማ የፓናል ውይይት አዘጋጅ ንዑስ ኮሚቴ ከውይይቱ ቀን አንድ ወር ቀደም ብሎ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የፓናል ውይይት አዘጋጅ ንዑስ ኮሚቴ ያስረክባል፡፡

5) ፎረሙ በሚካሄድበት ከተማ አቅራቢያ ከሚገኘው ዩኒቨርሲቲ በፓናል ውይይቱ ለመሳተፍ የሚመጡ ተማሪዎች የምሳ አገልግሎት በዩኒቨርሲቲያቸው የሚያገኙ ይሆናል፤፤ የሚከፈላቸው አበልም አይኖርም፡፡

ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር7

6) በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተቋቋመው የኢትዮጵያ የከተሞች ፎረም የፓናል ዝግጅት አስተባባሪ ንዑስ ኮሚቴ ውጪ ለፓናል ውይይት የሚያስፈልጉ የስቴሽነሪ ማቴሪያሎችና ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን በአዲስ አበባ እና ፎረሙ በሚካሄድበት ከተማ ለመጫን ለማውረድ፣ ለማስባጠር እና ለተሳታፊ ተወካዮች ለማከፋፈል በጉልበት ሥራ ያገለገሉ ሰዎች በሰሩበት ቀናት ብዛት መሰረት ዝርዝራቸው በፓናል ዝግጅት ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢ ተረጋግጦ እየቀረበ በቀን ብር 200 ሂሳብ ይከፈላቸዋል።

7) ለፓናል ጽሁፍ አቅራቢዎች፣ ለአወያዮች/ሞደሬተሮች እና የፓናል ተጋባዥ ፓናሊስቶች የሚከፈል የማበረታቻ ገንዘብ የበላይ አመራሩ በልዩ ሁኔታ በሚወስነው አግባብ የሚፈፀም ይሆናል።

8) የፓናል አወያዮች/ሞደሬተሮች እንደአስፈላጊነቱ በግገር እንዲቀርብ ይደረጋል።

## 11. ጥናታዊ ጽሑፉ አቀራረብና የማቅረቢያጊዜ፣

1) ለፓናል ውይይት ጽሁፍ እንዲያቀርቡ የተመረጡ ጽሁፍ አቅራቢዎች ጥናታዊ ጽሑፋቸውንከ 20 ገጽ ባልበለጠ ሰነድ አዘጋጅተው በሶፍት ኮፒ(በኢሜይል) ቢዘገይ የፓናል ውይይቱ ከመጀመሩ 21 ቀናትቀደም ብለው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የፓናል ዝግጅት አስተባባሪ ንዑስ ኮሚቴ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የጥናት ሰነዱ በ MS-Power point ተዘጋጅቶ የሚቀርብ ሲሆን፣ ይህ ለውይይት የሚቀርበው ፓወርፖይንት ሶፍት ኮፒ በኢሜይል ከአንድ ወር ቀድሞ ለፎረሙ አዘጋጅ ኮሚቴው መላክ አለበት። የ Power point አዘገጃጀቱም ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ያዘጋጀውን የውይይት ሰነድ ፓወር ፖይንት አቀራረብ ስታንዳርድ የተከተለ መሆን አለበት።

3) የጽሁፍ አቀራረብ ስታንዳርዱንየፓናል ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ ለተመረጡት ጽሁፍ አቅራቢዎች በደብዳቤ ያሳውቃል፣

4) የፓናል ዝግጅት አስተባባሪ ኮሚቴ የፓናል ውይይት የሚካሄድበት ቦታና የማቅረቢያ ፕሮግራም ለጥናታዊ ጽሑፍ አቅራቢዎችና ተሣታፊዎች ከበዓሉ ዝግጅት ቀደም ብሎ ያሳውቃል።

ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር8

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር * ኢትዮጵያ * ማህበር የሥራ ሂደት

## 12. የፓናል ጽሁፍ አቅራቢዎች ሊመሩባቸው የሚገቡ መርሆዎች

1) ጽሁፍ አቅራቢዎች ከአንድ በላይ ጥናታዊ ጽሁፍ ሊያቀርቡ ይችላሉ፣

2) ከአቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር ጥናታዊ ጽሁፎች በተወከለ ሰው እንዲቀርቡ አይፈቀድም፣

3) ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በውይይቱ መገኘት የማይችሉ ጽሁፍ አቅራቢዎች የፓናል ውይይቱ ከሚካሄድበት ቀን ቀደም ብለው ለውይይቱ አዘጋጅ ኮሚቴ ማሳወቅ አለባቸው፣

4) ለፓናል ውይይቱ የተመደበውን ጊዜ በአግባቡ ለመጠቀም እንዲቻል ጽሁፍ አቅራቢዎች በተመደበላቸው ሠዓት ውስጥ መቅረብ የሚችል ፓወርፖይንት አዘጋጅተው መገኘት አለባቸው።

## 13. የተሻሩ መመሪያዎች

ከዚህ ቀደም በተካሄዱ የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ላይ የፓናል ውይይቶችን ለማስፈጸም የወጡና ከዚህ መመሪያ ጋር ተቃርኖ ያላቸው መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል።

## 14. መመሪያው የሚጸናበት ቀን፣

ይህ መመሪያ ከጥቅምት 29 .ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚኒስትር